# ምርኮኛ

**ደራሲ ቆንጅት ብርሃን**
**ቅኝት  መስፍን ማሞ ተሰማ**

***<u>መንደርደሪያ</u>***




ደምና ዕንባ ተቀላቅሎ በብዕር ሲቀሰም ምንን ይወልዳል? ምርኮኛ! ምርኮኛ የደም መፅሀፍ ነው። የዕንባ መፅሀፍ። የአንድ ትውልድ ደም፣ የአንድ ትውልድ ዕንባ የተተረከበት የደም ዕንባ ታሪክ።

ምርኮኛ አንባቢን ምርኮኛው አድርጎ በትርክቱ ባህር እየደፈቀ፣ ትንፋሽ እስኪያጥር ነፍስ እስክትቃትት አካልና መንፈስን ረግጦ የሚገዛ፣ ሃያል የደም ዕንባ ታሪክ ነው - ያልታደለው ትውልድ ታሪክ።

ምርኮኛ በተደራሲ ነፍስያ ውስጥ የራሱን ነፍስያ ፈጥሮ እስከወዲያኛው የሚኖር ረቂቅ ህዋስ ያለው የትውልድ ታሪክ ትሩፋት ነው - ማን ይመስክር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ - እንዲሉ ጥንታውያኑ።

እና ምርኮኛን አንብቤ የአካልም የህሊናም ምርኮኛ ሆኜ ሰነበትኩ። ታሪከኞቹ ሲታገሉ ታግዬ፣ ሲታሰሩ ተቀፍድጄ፣ ሲገረፉ አቃስቼ፣ ሲረሸኑም ህቅ ብዬ - ነፍሴን ከስጋዬ ለይቼ። ኖርኩት ያንን ዘመን ዳግም ተወልጄ፣ ወጣትነቴን ምርኮኛ ውስጥ አግኝቼ።

ምርኮኛ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ አንድ ምዕራፍ የጨበጠውን የታሪክ ክስተት የሚያትት ነው። ዘመነ ኢሕአፓን።

መቼም 'ፍርድ እንደራስ ነው' እንዲሉ፣ ምርኮኛን ያላነበባችሁ መፅሀፉን አንብባችሁ ትፈርዱ፣ ያነበባችትሁም ሀቁን ትመሰክሩ ዘንዳ - እነሆኝ ምርኮኛ።

***<u>የትውልድ አደራ - ቅድመ ታሪክ</u>***

በፍሬህይወት ታሪክ ዙሪያ የተዋቀረው ምርኮኛ አስገራሚ ባህሪው የቀዳሚውን ትውልድ ታሪክ ቀጣዩ ትውልድ እንደምን ይመለከተዋል? የሚለውን ጥያቄ በረቀቀና በሰከነ አቀራረብ መመለሱ ነው።

የፍሬህይወትን ታሪክ ለብርሃን ለማብቃት አደራውን የተቀበለችው ስናፍቅ ትባላለች። የጤና ባለሙያ ናት። ነርስ። ስናፍቅ በዘመነ ኢሕአፓ ውስጥ አላለፈችም። ምናልባትም ያኔ እንቦቀቅላ ትሆን ይሆናል። ስናፍቅና ባልደረቦቿ በኤች አይ ቪ /ኤድስ/ የተጠቁ ኢትዮጵያውያንን ለመታደግ ከጤና ጣቢያ እስከ ቤት ለቤት ነፍስ አድን ዘመቻ በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈው የሚፋለሙ ወጣቶች ናቸው።

ወጣቶቹ በእነሱ ዘመን ለተስፋፋውና የብዙዎችን ለጋ ህይወት እየቀጠፈ ያለውን ደዌ ለመገደብ የሚያደርጉት ትንቅንቅ ራሱን የቻለ የውድቀትና የድል የትግል ታሪክን አቅፏል። እየታገሉ ነፍስ ሲታደጉ፣ ድል። እየታገሉ ህይወት ከእጃቸው ሲያመልጥ፣ ሽንፈት። እና ደግሞ በጎ ፈቃደኞች ናቸው፣ የወገኖቻቸውን እስትንፋስ ለማቆየት ወዶ ዘማቾች። እነሆ ፍሬህይወትንና ስናፍቅን ያገናኛቸው የህይወት ዑደትም ፍሬህይወት የ አልጋ ቁራኛ ስናፍቅ ደግሞ የነፍስ አድን አርበኛ ሆነው ነበር። እንቀንጭብ ከስናፍቅ ትረካ፣

*“እንደ ዕውነቱ ከሆነ ከኤች አይ ቪ እና ከማግለልና መድልዖ ጋር የተደረገው ትግል ከጦር ሜዳ ውሎ የሚተናነስ አልነበረም። ማግለልና መድሎው ተሰብሮ ያለመሸማቀቅ ህሙማን ቤት መግባትና መውጣት ስንጀምር የተሰማንም ኩራትና ደስታ እንዲሁ ነበር።*

*“እንግዲህ በዚህ አጋጣሚ ነበር የዚህ መፅሀፍ ባለታሪክ የሆነችውን ፍሬህይወትን ያገኘኋት።...”* ትለናለች ስንፍቅ። እነሆ ይህ ግንኙነትም ወጣቷን ስናፍቅና ፍሬህይወትን ባልጠበቁት ሁኔታ አቆራኛቸው። እናቅርብ ስናፍቅን፣

*“...አንዳንዶች ህሙማን የተለየ ስሜት ይፈጥሩብኛል። የትም ቦታ ሆኜ ትዝ ይሉኛል። ልክ እንደ ዘመዴ ሆነው ይታዩኛል። አንዳንዴ ከስራ ሰአትም ውጪ እንድጠይቃቸው መንፈሴ ያስገድደኛል። ከእነዚህ ህሙማን መኻል እኚህ ሴት አንዷ ናቸው።...”*

እርግጥ ነው ፍሬህይወትና ስናፍቅ በተዋወቁበት ሰሞን ስናፍቅ ፍሬህይወትን የምትጠራው በአንቱታ ነበርና ነው ‘እኚህ ሴት አንዷ ናቸው’ ማለቷ። ከተግባቡ በኋላ ግና እንደ ጓደኛ ነበር የሚጠራሩት።

ፍሬህይወት ማን ናት? በሚለው የጥያቄ ርዕስ የሚጀምረው የምርኮኛ ቅድመ ታሪክ ከፍሬህይወት ህይወት እየመዘዘ የሚያቀምሰንና በአንደኛ መደብ የትረካ ስልት የተዋቀረ /ራሷ ስናፍቅ የምታወጋን/ ቢሆንምና የፍርዬን የማታ ዕጣ /ህልፈቷን/ አስቀድማ ብታሳውቀንም ቅሉ፣ ፍሬህይወት ከየት ተነስታ በእንደምን ያለስ የህይወት ኮረኮንች ጎዳና ተጉዛ በህይወት ሽክርክሪት አጋጣሚ ከስናፍቅ እጅ እስከደረሰችበት ዘመን ያለውን ታሪኳን ለማወቅ በውስጣችን የሚያቀጣጥለው የማወቅ ሰደድ ሃያል ነው። ይህ አፃፃፍም የምርኮኛን ታሪክ በእጅጉ የተዋጣለት ታሪካዊ ሥነ ፅሁፍ አድርጎታል።

እንመለስ ወደ ስንፍቅ ወግ፣

*“ፀጥታ ሆነ፣ ፈራሁ በጣም ፈራሁ። እግዚአብሄር የአንድ ቀን ዕድሜ እንዲጨምርላት ደጋግሜ ጠየቅሁ።...በህይወትና በሞት መካከል ያለውን ቅርበት ሳስበው ተጨነቅሁ። አቤት እንዴት ይገርማል? ያችን ከህይወት ወደ ሞት የምንሸጋገርባትን ቅፅበት በርግጠኝነት መናገር የሚችል ማንም የለም...*

*“አደራዬን ልሰጥሽ ነበር ያስጠራሁሽ...”*

*“የምን አደራ ፍርዬ” አልኩ ልቤ በድንጋጤ እየተንደፋደፈች።*

*“ለልጆቼ የሚደርስ አደራ”*

*“ልጆችሽን እኔ እንዴት ላገኛቸው እችላለሁ ፍርዬ?”*

*"ግዴለሽም ልጆቹን ማግኘት አያስፈልግሽም። የአንቺ አደራ እነዚህን የተበታተኑ ወረቀቶች አሰባስበሽ ህይወት ዘርተሽባቸው ማሳተም ብቻ ነው..."*

እነሆ የትውልድ ታሪክ ለትውልድ ተላልፎ ምርኮኛ ተወለደ፤ የትውልድን የታሪክ አደራ በተረከበ ቀጣይ ትውልድ። የዚህ ተምሳሌነት ምን ይሆን? ብለን መጠየቅና መመርመር ግና የአንባቢያን ፋንታ ይሆናልና ምርምሩንና ተዛምዶውን ለታዳሚያን እተዋለሁ።

አንድ አባባል ከፍርዬ ንግግር ውስጥ ግን የሚከነክነንና ይበልጥ የሚያወያየን ይሆናል። ፍርዬ ለሰናፍቅ አደራዋን ስትሰጣት "ለልጆቼ የሚደርስ አደራ" ነበር ያለቻት። ለመሆኑ ፍሬህይወት ***"አብረውኝ ለታገሉትና በህይወት ለተረፉት ጓዶቼ የሚደርስ አደራ ከማለት ይልቅ ለልጆቼ የሚደርስ አደራ ለምን አለች?"*** ፍሬህይወት የትግልና የመስዋዕትነት ታሪኳን በአደራነት ማስተላለፍ የፈለገችው ከእሷ ትውልድ በኋላ ለመጣው ትውልድ ነው። ለምን? ደርግ አምባገነን መንግሥት ነበር። ፍሬህይወትና ጓዶቿ የታገሉት አምባገነንነትን ለማስወገድ ነበር፤ አልቻሉም። ደርግ ወደቀ። ሌላ ጭራቅ አምባገነን ተተካ። እና ፍሬህይወት በስንፍቅ ድልድይነት ማስተላለፍ የፈለገችው መልዕክት ምንና ለማን ነው? ታዳሚያን በአርምሞ ሊመረምሩት ይገባል።

እርግጥ ነው እነፍርዬ የታገሉለት ዓላማና ግብ ውጤት አልባ ሆኖ ተደምድሟል። ሀቅ ነው እነፍርዬን አስተባብሮ ያታገላቸውና ህይወታቸውን የገበሩለት ድርጅት በህይወት በተረፉት በእነፍርዬ በራሳቸው ዕምነት ለማክተሙ ምስክርነት ሰጥተዋል።

ይሁንና ታሪካቸው፣ የትግልና የመስዋዕትነት ትግላቸው ሳይበረዝ፣ ሳይከለስና ሳይንቆለጳጰስ የነበረው እንደነበረ ለትውልድ ተላልፎ በምርኮኛ ሲተረክልን ውስጣችንን የሚቆጠቁጥ፣ ህሊናችንን የሚቆነጥጥ ስሜት ይወረናል።

የኢሕአፓ ትግል አምባገነናዊውን ወታደራዊ መንግሥት መገርሰስና በምትኩ ሕዝባዊ መንግሥት መመስረት ነበር። ሕዝባዊው መንግሥት ምን ይመስላል? ለሚለውም ርዕዮተ ዓለማዊ ፕሮግራምና መመሪያ ነበረው። በዚያ ርዕዮተ ዓለማዊ መሰረት ላይ የሚገነባው የላባደር መንግሥት በተጨባጩ ዓለም ገቢራዊነቱና ላባደራዊነቱ 'ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ' ሊሆን ይችል እንደነበርም የሌሎች ሶሻሊስታዊ/ኮሚኒስታዊ ሀገራት ተመክሮ አሳይቶናል፤ ምንም እንኳን በዘመኑ ለኢህአፓውያኑ የተከሰተላቸው ባይሆንም ቅሉ።

ማርክሳዊ ሌኒናዊው ርእዮት እንደ ኢትዮጵያ ላለች በኢኮኖሚዋ ላልበለፀገችና ድህነትና ኋላ ቀርነት መለያዋ ለሆነች ሀገር የማይሰራ የመሆኑ ዕውነታም ከኢሕአፓ መመታት በኋላ በህይወት ለተረፉት ኢሕአፓውያን ከትግሉና ከመስዋዕትነቱ ጎራ ለመገለላቸው፣ ድርጅቱም እንደ ጥንቱ ሀይልና ህዝባዊ መሰረት ኖሮት ለመነሳት ላለመቻሉ (ከሌሎች ምክንያቶች በተጨማሪ) ቀንደኛው ምክንያት ይሆናል።

እንመለስ ወደ ሰናፍቅ ትረካ፤

*"የነፍርዬን ወቅትና አመለካከት ለመረዳት እነርሱ በትግሉ ወቅት ይከተሉት የነበረውን ፍልስፍና ለማወቅ ማንበብ ጀምሬያለሁ። ይህ ደግሞ ከነፍርዬ ልወስድ የሚገባኝ አንዱና ትልቁ ተሞክሮ መሆኑን እንድቀበል አደረገኝ። እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ በማወቅና በመነጋገር ላይ ማነፃቸውን አደንቃለሁ፤ የተቀበሉትን ስቃይ ሁሉ እንዲቀበሉ ያፀናቸው አውቀውና አምነው መግባታቸው ይመስለኛል። እናም የእነርሱን አስተሳሰብ በደንብ ለመረዳት እንድችል ጥርሴን ነክሼ፣...በቁርጠኝነት አነበብኩ።...ባነበብኩ ቁጥር ደግሞ*

*እየሳበኝ እመሰጠኝ ሄደ። ካሰብኩት በላይ አነበብኩ። ለህይወቴ ሁሉ የሚሆነኝንም የማንበብ ልምድ አዳበርኩ።”* ትላለች ስናፍቅ።

ከዚህ የስናፍቅ አገላለፅ የተለያዩ አንጓዎችን መዝዘን በየፈርጁ ማበራየት እንችላለን። ጥቅል ሀሳቡ ሲፍታታ ብዙ ያወያያልና። በሁለት ነቁጦች ላይ ብቻ እናትኩር።

<u>አንድ፤</u>

*“…ማንበብ ጀምሬያለሁ። ይህ ደግሞ ከነፍርዬ ልወስድ የሚገባኝ አንዱና ትልቁ ተሞክሮ መሆኑን እንድቀበል አደረገኝ።”*

ማንበብ  የዕውቀት ምንጭ ነው። ጨቋኝንና አምባገነን አገዛዝን መንግሎ ለመጣል ብቻ ሳይሆን በምትኩ በመልካም አስተዳደር ላይ የተገነባ፡ የዜጎችን ሁሉ መብት፤ ነፃነትና እኩልነት የሚያከብርና የሚያስከብር፤ በህግ የበላይነት የሚያምንና የሚገዛ የህዝብ ድጋፍና አመኔታ ያለው መንግሥት ለማቆም በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ዓላማና ግብ ይኖር ዘንዳ ግድ ነው።

እኒያ የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን የትግል ፅናታቸውና ዕምነታቸው መሠረት ማነብነብ ሳይሆን ማንበብ፤ መከተል ሳይሆን መመርመርና ማመን፤ መነታረክ ሳይሆን መወያየት…ነበርና ወጣቷ ስናፍቅ ይህንን ከነፍሬህይወት ጠንቅቃ ተገንዝባለች። ስለተገነዘበችም ከቀዳሚው ትውልድ የትግል ታሪክ ልወስድ የሚገባኝ ‘አንዱና ትልቁ ተሞክሮ ማንበብና ማወቅ ነው’ ትላለች።

እነፍሬህይወት ዘርፌ ብዙ መስዋዕትነትን በመክፈል አምባገነናዊውን የደርግን አገዛዝ በሕዝባዊ መንግሥት ለመተካት ቢታገሉም አልቻሉም። ተሸነፉ። ያ! እነፍሬህይወትን አሰባስቦ ያታገለው ኢሕአፓም እንደ ኢሕአፓነቱ አከተመ። ደርግን የጣሉት በጎጥ ፖለቲካ የተደራጁት ህወሃትና ሻዕቢያ ናቸው። ህወሃት አዲስ አበባ በኢህአዴግ ካባ መንግሥት ሲያቆም መንትያው ሻዕቢያም አሥመራ ላይ መሰል መንግሥት ተከለ። ይሁንና ሁለቱም ጭርሱን ከደርግ የበለጠ አምባገነኖችና አፋኞች ሆኑ እንጂ በሕዝብ ድምፅ የሚያምኑ ሕዝባዊ መንግሥታት አልሆኑም።

በአንድ ዕብሪተኛ አምባገነን ትገዛ የነበረች አንዲት አሃዳዊ ሀገር በሁለት ወደር አልባ አምባገነን መንትዮች ሁለት ሀገራትና ሁለት ህዝቦች ተብለው በየፊናቸው በታሪካቸው ታይቶ በማይታወቅ መንገድ የቁም ስቅላቸውን እያዩ ይገኛሉ። የኤርትራ ህዝብ በመልካም አስተዳደር ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት አላገኘም። እንደውም አቶ ኢሳያስ በቅርቡ በምድረ ኤርትራ ቢያንስ ለሚመጣው 40 ዓመት ምርጫ ብሎ ጣጣ እንደማይኖር ተናግረዋል። ሻዕቢያ የኤርትራን ህዝብ ሰብዓዊ መብቶች መርገጥ ብቻ ሳይሆን ህግና ፍትህ አልባ እስርና ግድያ ዴሞክራሲን በሚጠይቁ ኤርትራውያን ላይ ሁሉ በከፋ መልኩ ያካሂዳል። ሻዕቢያ ለኤርትራ ህዝብ ሠላም ከቶም አላመጣም። አምሳያው ህወሃትም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው ግፍና በደል እንደ ሻዕቢያ ወንድሙ ነው። አቶ መለስ ዜናዊም መተካካት በሚለው የህወሃት መሰሪ የሥልጣን ኮርቻ መቀባበያ ፖሊሲያቸው በሸፍጠኛ ምርጫ ስም ወደፊት ቢያንስ ለ40 ዓመት የሚሆን መሰናዶ ማጠናቀቃቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው። አዲስ አበባና አሥመራ ላይ በተቀመጡት የዘመኑ ጭራቅ ፀረ ዲሞክራሲ፤ ፀረ እኩልነትና  ፀረ ሠላም በሆኑ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ መሪዎች ሁለቱም ህዝቦች የቀን ጨለማ ውጧቸው ዘመናትን እያስቆጠሩ ናቸው። አሥመራና አዲስ አበባ ላይ የከተሙትም መሪዎች ለጊዜው የሚገፋፉ የሚመስለው ማግኔታቸው የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ዘላቂ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥቅም

ለማስከበር ከንድፈ ሀሳባዊ ዕቅድ አልፎ ወደ ተግባር በሚያመራ ጉዳይ ላይ በማንኛውም ሰአትና ቀን የተገፋፋ የሚመስለው ተፈጥሯዊ ማግኔታቸው ከመቅፅበት ተጣብቆ በአንድ እንደሚቆሙ ለአፍታ እንኳን ልንክደው አይገባም። ህወሃትና ሻዕቢያ የአንድ ሳንቲም ሁለት አካል የሚያደርጋቸውም ማግኔታዊው የተፈጥሯቸው መሰረቱ ፀረ ኢትዮጵያነታቸው ነውና!! ይህ እንደ ፀሐይም የጋለ እነደ አለትም የጠጠረ ደረቅ ሀቅ ነውና፣ ሀቅ ያንቅ እንዲሉ፣ እንግዲህ ጆር ያለው ይስማ! ልቡናም ያለው ሀቁን ይመርምር!!

እንቀጥል ምርኮኛን፣

እነፍሬህይወት ከታገሉትና ካሳለፉት የደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ በበለጠ በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችና የህብረተሰቡ ክፍሎች በከፋ ማነቆ ውስጥ እንጂ የሚገኙት ብሩህ ተስፋ በሚታይበት መልኩ ከቶም አይደለም።

አምባገነኖችና አፋኞችም ከሌሎች አምባገነኖችና አፋኞች ይማራሉና ህወሃት መራሹ ኢህአዴግም ከኮሎኔል መንግሥቱ አወዳደቅ አያሌ “ሥልጣን አሰንባች” ትምህርቶችን ቀስሟል። ህወሃት/ኢህአዴግ ከደርግ ይልቅ የረቀቀና የተወሳሰበ የአገዛዝ ሥልት ያለው ብቻ ሳይሆን መርዙም ሥር የሚሰድና ለትውልድም የሚተርፍ እንዲሆን ተደርጎ የተቀመመ ነው።

በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ቀንበር ሥር ያለው ወጣት ይህንን መርዝ ማምከን የሚችለው አደገኛነቱ ህልውናውን /ማንነቱን/ እና መኖሪያውን /ሀገሩን/ የሚያሳጣው እስከመሆን ድረስ የሚዘልቅ ስለመሆኑ ጠንቅቆ ሲረዳና ሲያምን ብቻ ነው። በአደገኛ ፍጥነት እየተበረዘ ያለውን የማንነቱን  ታሪክ ለማጠጥራት ደግሞ ማንበብ፣ ማመዛዘንና በአመክኗዊ ሚዛን ላይ የቆመ የታሪኩ ግንዛቤ ሊኖረው ግድ ይላል። ይህም ራዕይ እንዲኖረውና ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስ ጠንቅቆ እንዲረዳ ያደርገዋልና። መነሻው የፀና ሆኖ መድረሻው ላይ ለመገኘት ባለው ውጣ ውረድ ውስጥም የዓላማና የመንፈስ ፅናቱን የሚሸረሽር ሃይል ከቶም ሊኖር አይችልም።

በተለይ ከ1966 ዓ/ም ጀምሮ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዋር የቀየረው ወጣቱ ትውልድ ነው። ጭቆናንና አምባገነንነትን ተሸክሞ ይዘልቅ ዘንዳ አይቻለውም ወጣቱ። የነገይቷን ኢትዮጵያ መፃዒ ዕድል የሚወስነውም የወጣቱ ትውልድ ተሳትፎ ነው። የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ሊገረሰስ የሚችለውም ወጣቱ ትውልድ ሀገራዊ በሆነ አሃዳዊ የድርጅት ጥላ ተማክሎ ሙሉ ተሳትፎና የትግል ፅናት ሲኖረው ብቻ ይሆናል። ምርኮኛን ከዚህ አንፃር አንብበው ለሚመረምሩም መልዕክቱ ጥልቅና ብርቱ ነው።

እነፍሬህይወትን አስተባብሮ ያታገለው የዛን ዘመኑ ኢሕአፓ ለድል መብቃት ባይችልም በድፍን ጦቢያ ወጣቱን፣ ጎልማሳውን፣ ምሁራኑን፣ ወታደሩን፣ በተለያዩ የሙያ መስኮች የተሰማሩ ዜጎችን፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን፣ አዛውንቶችንም ጭምር በማቀፍ፣ በማነቃነቅና በማታገል ረገድ ምናልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ፓርቲ ሳይሆን ይቀራል? ከዛን ዘመኑ አሕአፓ ትግልና ሽንፈትስ ለዛሬው ትግል የምንማረው አንዳች ቁብ አይኖር ይሆን?

እየህ ላይ ነቁጥ አንድን ሽብ እናድርግና አንጓ ሁለትን እንምዘዝ - ከስናፍቅ ትረካ።

**<u>ሁለት፤</u>**

*“.../ኢሕአፓውያኑ/ እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ በማወቅና በመነጋገር ላይ ማነፃቸውን አደንቃለሁ፣ የተቀበሉትን ስቃይ ሁሉ እንዲቀበሉ ያፀናቸው አውቀውና አምነው መግባታቸው ይመስለኛል።...”*

ይህ አንዳች ቅንጣት ጉድፍ የሌለው ሀቅ ነው። የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን ያንን ሁሉ ስቃይና መከራ ለመቀበል ያፀናቸው ዕውቀቱና ዕምነቱ ስለነበራቸው ነበር። ይህ የስናፍቅ ጥልቅ ግምገማ በቁጥር አንድ ያበራየነውን የሚያጠናክር ሆኖ ይገኛል።

በዚያን ዘመን አሕአፓን ተቀላቅለው ወደ ትግሉ ጎራ የገቡት ሁሉ በድርጅቱ ፕሮግራምና ዓላማ አምነውና ተፈትነው (ለምሳሌ በጥናት ክበብ ወዘተ) እንጂ ድርጅቱ በማን ወይንም በእነማን ይመራል? በሚለው የአሁን ዘመን ወደ ድርጅት መቀላቀያ ግለሰባዊ መለኪያ ላይ ተንተርሰው አልነበረም።

በአሁን ዘመን እያንዳንዳችን ለራሳችን ህሊና ታማኝ እንሁንና የሚከተለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለውስጣችን እናቅርብ፤ *“ብዙዎቻችን ድርጅትን የምንቀላቀለው ዓላማና ግቡ ከውስጣችን ተዋህዶና ሰርፆ በድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራምና መርህ ላይ በዕውቀት የታነፀ ዕምነት ኖሮን ነውን ወይስ በየድርጅቶቹ መሪዎች ላይ ባለን ግላዊ አመለካከትና አቋም?”* ለመልሱም ልቦናችንን እናዳምጥ።

እርግጥ ነው ለዚህ ዓይነቱ መሰረት ያልያዘ የድርጅት አባልነት ያደረሱን ቀዳማይ ክስተቶች ተፈጥረው ሊሆን ይችላል። መዘዛቸው ግን በእጅጉ እየጎዳን መሆኑን ልንገነዘብና መፍትሄም ልናፈላልግለት ይገባል።

አንጓ ሁለትን በዚህ ዘግተን፤ እንመለስ ወደ ምርኮኛ - ወደ ስናፍቅ ቅድመ ታሪክ ትረካ።

*“ፍርዬን የሁለት ጦርነቶች ምርኮኛ ሆና አገኘኋት...ፍርዬ ጀግና ነች፣ በአንደኛው ጦርነት ቁስለኛ ሆና ቆየች፣ ሁለተኛው ጦርነት ግን ህይወቷን ነጠቃት። ፍርዬ ዛሬም ጀግና ነች።...”* ትለናለች ስናፍቅ ፍሬህይወትን በምታስተዋውቅበት ‘ፍሬህይወት ማን ናት?’ ቅድመ ታሪክ።

ምርኮኛ በደርግ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ በቀይ ሽብር በገፍ ያለቁትን፤ በእስር ቤቶች ወደር አልባ ቶርቸር የደረሰባቸውን፤ ለዓመታት እስር ማቀቃ፤ ለስደት፤ አሲምባ ብለውም ወጥተው ለቀሩት...ለእኒህ ሁሉ የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን ታሪካቸውን ሳያውገረግር ስለትግላቸውም ገድል ሳይመፃደቅ ለትውልድ የሚተላለፍ  የፅሁፍ ሀውልት ያኖረ መሆኑን የምንረዳው በፍሬህይወት ተምሳሌነት...’ፍርዬ ዛሬም ጀግና ነች’ በማለት የዘከረልንን ሀቅ ስናነብ ይሆናል።

ንዑስ ርዕሳችንን ስንሸክፍም ከ’ፍሬህይወት ማን ናት?’ ቅድመ ታሪክ የሚከተለውን በመንቀስ ነው፤

*“የፍርዬን ሞት መቀበል ግድ መሆኑን ባምንም፣ ሌሎች በርካቶች መሞታቸውን ባውቅም ተፈተንኩበት።...ፍርዬ ሞታ ከመቃብር በታች ውላለች። እኔ ግን አደራዬን አልበላሁም። እንባ በጉንጮቼ እየወረደ የፍርዬን የተቆራረጡ ፅሁፎች ደጋግሜ አንብቤያቸዋለሁ። ተገጣጥመው ትልቅ ታሪክ ሊወጣቸው እንደሚችል ጥርጥር የለኝም። ግን ፍርዬን*

*ልጠይቃት የምፈልጋቸው በርካታ ጥያቄዎች ነበሩኝ፤ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጠኝ ሀይል ከየት አባቴ አገኛለሁ?”*

<u>ምርኮኛ - ወፍ በረር ዳሰሳ</u>

ስድስት አበይት ክፍሎች በአራት መቶ ዘጠና አንድ ገፆች የተካተቱበት ስፋትና ጥልቀት ያለው መፅሀፍ ነው - ምርኮኛ። ከዚህ ውስጥ ሃያ ሰባቱ ገፆች ‘ፍሬህይወት ማን ናት?’ በሚል ስናፍቅ ያቀረበችልን ቅድመ ታሪክ መተዋወቂያ ሲሆን ከክፍል አንድ እስከ ክፍል ስድስት የሚዘልቁት 467ቱ ገፆች በኢሕአፓውያኑ ታሪክ የተሞላ ነው። የህትመት ዘመኑስ? ሁለት አማራጮች አሉ። በሽፋን ገፁ 2002 ዓ/ም በውስጥ ገፁ 2003 ዓ/ም። የተፃፈበትና የታተመበት ይሆን? ሆነም አልሆነም፤ የህትመት ዘመኑ ቀደመም ዘገየም የምርኮኛን ምርኮኛነት ግን አይቀንስም።

ምርኮኛን ልዩ የሚያደርገው ባህሪ በጥንቱ በጠዋቱ ኢሕአፓና ኢሕአፓውያን ላይ ብቻ መሰረቱን ጥሎ ቤቱን የገነባ በመሆኑ ነው። ምርኮኛ ከፕሮፓጋንዳ የፀዳ የትግልና የመሥዋዕትነት ታሪክ መስታየት ሆኖ በመፃፉ ለተነባቢነቱና ለመሳጭነቱ፤ ብርቱ ነው ጉልበቱ።

የቋንቋው አሰካክና አወራረድ፤ የገላጭነት አቅምና መስህብነቱ፤ የታሪኩ ውቅረትና የትረካው ፍሰት፤ አጓጊነቱና ልብ አንጠልጣይነቱ…ደራሲ ቆንጅት ብርሃንን እጅዎት ይባረክ ደግመው ደጋግመውም ለመፃፍ ያብቃዎት ብለን እንድንመርቃቸው ያደርገናል። ተፈጥሮን፤ አካባቢን፤ ድርጊትንና ሁነቶችን እንደፎቶግራፍ በምናባችን ተቀርፀው እንድናያቸው የማድረግ ሃያል ሥነፅሁፋዊ ብቃት አለው፤ ምርኮኛ።

እነሆ ለናሙና የነቀስነውን እንደሚከተለው ያነቧል፤

*“በምዕራቡ አድማስ ስር ልትጠልቅ እያሽቆለቆለች፤ ድብዝዝ እያለች በተራራው አናት ላይ ጉብ ያለች የምትመስለው ፀሐይ የምትፈነጥቀው ወርቃማ ቀለም ለአካባቢው የሚሰጠው ውበት በበላይሁን ልብ ውስጥ ልዩ ቦታ አለው።…*

*“…ከተራራዎቹ በስተግርጌ ያለው ረጅም ገደል ጎበዝ መሀንዲስ የነደፈው ህንፃ ይመስላል። ከገደሉ አናት ላይ እየተወረወረ የሚንቧቸው ውሃ ድምፁ ባይሰማውም ዕይታው ብቻ መንፈሱን ያማልለዋል። ፏፏቴው ተወርውሮ ከሚያርፍበት ባሕር ረጋ ብሎ ስርዓት ባለው መልኩ እየፈሰሰ ከትልቁ ወንዝ ጋር ይቀላቀላል። ትልቁ የጀማ ወንዝ ከየሥፍራው ገባሮቹን እየተቀበለ በሰፊ መልካው ያካትትና በእርጋታ ሲጓዝ በርቀት ለሚመለከቱት የበላይሁን ዐይኖች ረጅም መቀነት ይመስላል።*

*“ከተራራው በስተጀርባ ለመደበቅ የምታሽቆለቁለው ፀሐይ ቀይ ጨረር ኩል ከመሰለው የጠራ የበጋ ወንዝ ውሃ ላይ ሲያርፍ የሚፈጥረው ሕብረቀለም ልብን ይሰርቃል።”*

እንዲህ በመሳሰሉ የገላጭነት ውበታቸው ምናብን በሚያመጥቁ፤ በሥነፅሁፍ በደመቁ ተፈጥሮን፤ ክስተትን፤ ድርጊትን እንደ መስታየት በሚያሳዩ አገላለፆች የተሞላ ነው - ምርኮኛ።

እንቀጥል ዳሰሳችንን፤

አሃዱ ብለን ምርኮኛን ማንበብ ስንጀምር የታሪኩን እንብርት የጨበጥን ቢመስለንም የትርክቱ ሂደት ከየት ተስፈንጥሮ የት እንደሚያርፍ፣ ማንንስ ተዋውቀን ምን እንደሚገጥመን፣ ስለ እነማን አዝነን ስለ እነማንስ እንደሚጨንቀን መጠንቆል የምንችል ባለመሆኑ በየገፁ የሚንጠለጠል ልባችንን ለማሳረፍ፣ በየታሪኩ የተወጠረ ስሜታችንን ለማርገብ ከገፅ ወደ ገፅ የአፈተላለክ ፍጥነታችን ለራሳችንም ግርም ይለናል።

ትረካው በአንድ ውሱን ተግባር ወይም ሂደት ላይ ብቻ ያጠነጠነ ባለመሆኑም በየክፍሎቹ ሁሉ ጦዘው የሚያጦዙ ጡዘቶች የሞሉበት ነው - ምርኮኛ። ትረካው ወደፊትና ወደኋላ እየወሰደና እየመለሰ ነፍስያችንን በስሜት ውጥረት እንዳንገላታት ከዳር ያደርሰናል ምርኮኛ - ከታሪኩ ማሳረጊያ።

ታሪከኞቹ /ኢሕአፓውያኑ/ ህያው ናቸው፣ አቀራረፃቸው። የሚታዩ፣ የሚዳሰሱ፣ የሚጨበጡ። የምናውቃቸው ከጎረቤት፣ ከት/ቤት፣ ከመሥሪያ ቤት፣ ከሰፈር። የምናስታውሳቸው አጎቶች፣ አክስቶች፣ ወንድሞች፣ እህቶችና ጓደኞች። የምናከብራቸው እናቶች፣ አባቶች፣ መምህራን እና ሙያተኞች።

ፍሬህይወት፣ በላይሁን፣ አንተነህ፣ ሚሚ፣ ቅዱስ፣ ቃላብ፣ ዳኙ፣ ታሪኩ፣ ፈቃደ፣ ሚስጢረ፣ ምዕራፍ፣ ሄዋን…ወ/ሮ ስርጉት፣ የበላይሁን እናት…እኒህንና እጅግ በርካቶች የምርኮኛን ታሪከኞች እናውቃቸዋለን፣ እናያቸዋለን፣ እናስታውሳቸዋለን፣ እንጨነቅላቸዋለን፣ ቅርባችን ናቸውና።

ለወ/ሮ ስርጉት የእናታችንን ያህል እንጨነቅላቸዋለን፣ አብጠርጥረን እናውቃቸዋለንና። ለበላይሁንም እናት እንዲሁ። እንቀንጭብ ናሙና፣

*“ግቢው ፀጥ ረጭ ብሏል፣ ወ/ሮ ስርጉት መንፈሳቸው እንደተረበሸ ነው የዋሉት፣ ሥራ መሥራት እንኳን አልሆን ብሏቸው ሲወጡ ሲገቡ ቆዩና አልጋቸው ላይ ጋደም አሉ። በፍፁም የሚያርፍ ስሜት የላቸውም፣ እንደገና ተነሱና አገልግላቸውን አንስተው ወደ በረንዳው ወጡ። ጥጡን በደመነፍስ ከአገልግሉ ያወጡና አረጋግፈው እክዳኑ ላይ ያስቀምጣሉ። አገልግሉ ውስጥ ያለው ጥሬ ጥጥ ሲያልቅባቸው ደግሞ መፈልቀቅ ጀመሩ።*

*“…ሚሚን ከሃሳባቸው ማውጣት አልሆነላቸውም። ሁሌም በዐይነህሊናቸው የሚመለከቷት ተርባ፣ ደክሚት፣ የተቦጫጨቀ ልብስ ለብሳ…አንዳንዴ ደግሞ ወድቃ ነው። ሚሚና አብረዋት ያሉ ወጣቶች በየጫካውና በየተራራው የሚሄዱ ይመስላቸዋል። ሁሌም ከአቅሟ በላይ የሆነ ነገር ተሸክማ አደናቅፏት የምትወድቅ፣ ጓደኞችዋም ሳያይዋት ትተዋት የሚሄዱ ይመስላቸውና ‘ልጄን’ ይላሉ ሳያስቡት።…በሃሳባቸው መሆኑን ሲያስታውሱ ደግሞ፣ ‘በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ’ አሉና አማትበው ተቀመጡ፣ እንደገና ጥጣቸውን አነሱ፣…”*

እነሆ በዚህ ገለፃ ወ/ሮ ስርጉትን በገሀዱ አለም እንደምናያቸው ሁሉ ይታዩናል። እናት ናቸው፣ ልጃቸው ኢሕአፓን ብላ ወጥታ ቀርታለች፣ ቀዩን ጦር ልትቀላቀል ሄዳለች። ይህንን የእናት አንጀት እንደምን ችሎት ይኖራል? በቀን ቢቃዡ፣ በሃሳብ ቢነሆልሉ ማን ይፈርድባቸዋል? እና ጭንቀታቸው ይጨንቀናል። ሀዘናቸው ውስጣችንን ይቦረቡረዋል። ከቶም ሳይታወቀን በዐይነ ህሊናችን እኛን በሚሚ ቦታ ወ/ሮ ስርጉትን ደግሞ በእናታችን ቦታ እናስቀምጥና ስለእናታችን ሀዘናችን ይበረታል፣ ህቅ ብለን ማልቀስ ይቃጣናል። ምናልባትም እንደ ሚሚ ወጥተው የቀሩ እህቶች ጎረቤቶች አክስቶች…እናውቅ ይሆናል። እና ባር፣ ባር ይለናል። ወይዘሮ ስርጉት ያባቡናል፣ በእሳቸውም ውስጥ አሻግረን አእላፍ እናቶች ይታዩናል። ልጆቻቸው በየአስፋልቱ፣ በየቤተክርስቲያናቱ፣ በየአደባባዩ ለሌሊት ቁር ለቀን ሀሩር ሬሳቸው በቀይ ሽብር የተሰጡት ሁሉ በአይናችን ስር ይሄዳሉ…እና

ምርኮኛ እንዲህ እያዋዛ የዛን ዘመኑን፤ የሩቁን፤ የተረሳውን የኢሕአፓውያኑንና የቤተሰቦቻቸውን ታሪክ አመሳጥሮ ሲተርክልን…ነፍሳችንን ይዞት ጭልጥ ይላል። ወይ ዘመን? አወይ ጦቢያ! አወይ ትውልድ! አወይ እልቂት! እያልን ገፅን በገፅ እናጣፋለን…

እንግታና ይህንን፤ እንቀጥል ወፍ በረር ቅኝታችንን፤

ምርኮኛ የፍቅርም መፅሀፍ ነው። ትግል፤ መስዋዕትነት፤ እስር፤ ስደት ፍቅርና ትዳር እንደ ድርና ማግ ተጠላልፈው፤ ተቆላልፈው የምናገኝበት። ፍቅር በትግል ዘመን። ፍቅር በ እስር ዘመን። ፍቅርና ትዳር ከእስር ዘምን ማዶ። ጉደኛ ነው ምርኮኛ። ማን ማንን አፈቀረ? ማንስ ማንን እንዳፈቀረ፤ በልቡናው መቅረዝ ውስጥም ፍቅሩ እንደተዳፈነ ቀረ? ለምን? ማን በለስ ቀንቶት የፍቅር አምላክ እንትፍትፍ ብሎለት ከማን ጋር ተቆራኘ? የታደለውን የምርኮኛ አንባቢን የሚጠብቁት የድግስ አይነቶች ናቸው። እነሆ ወደ ድግሱ ተጋብዛችኋል። የልብ እስኪደርስ መኮምኮሙ የእናንተ ድርሻ ነው። በእኛ በኩል እነሆኝ ቅምሻ፤

*"…ወደ ደረቱ አስጠግቶ አቀፋትና በሚንቀጠቀጡ ከንፈሮቹ ሳማት። ለዘለዓለም ከእቅፉ እንዳትወጣ የሚያደርግ ይመስል የበለጠ ወደደረቱ አስጠግቶ አቀፋት። ትንፋሿ ቁርጥ ቀርጥ እስኪል፤…ጉንጮቿ እስኪቀሉና ቲማቲም እስኪመስሉ ድረስ።*

*"ከዚያ በኋላ ቀና ብላ ልታየው አልደፈረችም፤ አፈረችው። ማንም ስሚት አያውቅም፤ ቀድሞውንም ከወንድ ጋር እንዲህ ዓይነት ቅርርብ ኖሯት አያውቅም።…በቀስታ ከንፈሮቿን በእጇ የዳበሰቻቸው ያበጡ መሰሏት ነበር። ግን ምንም የማበጥ ምልክት አላገኘችም። ድርጊቷ ለራሷ ገረማት…"*

በፍቅር ገነት ውስጥ ገብተው የፍቅርን እንጆሪ የተጋሩት እነማን ይሆኑ? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። መልሱን እንሰጥ ዘንዳ እኛ አይቻለንም። በትግልና በፍቅር አውድማ ውስጥ ምርኮኛ የሚሰጣችሁ ምልሶች በርካቶች ናቸውና ወደዛው አውድማ እንመራችኋለን፤ ቅኝቱን ስትጨርሱ።

ቀጣዩን ግን እንቀጥላለን፤

የምርኮኛ ተዓማኒነትስ? እየህ ላይ ደራሲ ቆንጅት ይጠየቃሉ። ምርኮኛ ልቦለድ ነው ዕውነተኛ? ወይስ በዕውነተኛ ታሪክ ላይ የተገነባ ሆኖም ደራሲዋ የታሪኩን ክፍተት የሞሉት? ለምን በግልፅ አልነገሩንም ደራሲ ቆንጅት? …ይህ ታሪክ ዕውነተኛ ታሪክ ነው…ብለው ለምን አልፃፉልንም?

በእኛ በኩል ግን እርግጥ ነው አንጠራጠርም የምርኮኛን ዕውነታ። እንላለን እኛ፤ አይሆንም ከቶም ሊሆን ልቦለድ ምርኮኛ! እናንተ እነማን ናችሁ? ትሉን ይሆናል። አዎን እኛ የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን፤ የትውልድን ፍዳ የተጋትን፤ ከሞት የተረፍን፤ ከዘመናት እስር የወጣን፤ እንደ ጨው ዘር በመላው ዓለምም የተበተንን፤ አሃዛችንም የትየለሌ። እና ውስጣችንን ብቻ እያዳመጥን ዝምታን መረጠንና ዝም አልን፤ ለዓመታት። ዝም አይነቅዝም - እንዲሉ። ዝምታችን ለምን? የውስጣችንን ህመም፤ የአካላችንን ጠባሳ፤ የህሊናችንንም ሰቆቃ ማን ሊሰማን ማንስ ሊረዳን አልንና ዝምታን መርጠን ዝም አልን። ስለኢኒያ ስለሞቱትና የግፍንም ፅዋ ስለተጋቱት በየእስርቤቶችም ውስጥ ህሊናቸውን ስተው ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ሆነው ስለቀሩት ክብር ብለን፤ ዝም አልን! ዝም አልነው ለአመታት ስንቱን እየሰማን እንዳልሰማን ስንቱን እያን እንዳላየን። ዝም አልን፤ እንቶ ፈንቶ ላንፅፍ ብዕራችንን ካፎቱ ከትተን፤ ከአንደበታችንም ተቆጥበን ዝምታን መርጠን ዝም

አልን። ዝም አልን ለዘመናት፤ በሞተው የዚያን ዘመን ኢሕአፓ ትግል ላንፈላሰፍ በሰማዕታቱም ስም ላንጠላለፍ! የሰማዕታቱንም መሥዋዕትነት ላለማጉደፍ እናም ላለመጎዳደፍ!

**ትላንት በሞትንለት በተጋዝንለት የቁም ስቅላችንን ባየንለት ድርጅት ስም - በስማችን - የሚፃፈውና የሚከወነው ሁሉ እያሳዘነንና ቆሽታችንን እያደበነው ደግሞም በየአካባቢው ስማችንን -ኢሕአፓነትን - ባነገቡት የምናየው የሞራል የሶሻልና የፖለቲካ ምግባረም እያሳፈረን ሰሚ በሌለበት ምድረበዳ ማን ሊሰማን ዕውነታችንንስ ማን ሊረዳን አልንና ዝምታን መርጠን ዝም አልን፤ ዝም አይነቅዝም ብለን። ለሁሉም ጊዜ አለው አይደል እሚለው መጣፉ? እንግዲህስ ድምፃችን ይሰማ! ቃላችንም ይነበብ! እነሆ ዛሬ በአደባባይ በይፋ እንመሰክራለን እኛ ስለምርኮኛ፤ በታሪኩ ውስጥ ነበርንበትና፤ በዚያን ዘመን ህይወት ውስጥም አልፈናልና። የሞትንለት፤ የታሰርንለት፤ አካለ ጎዶሎ የሆንንለት፤ ህሊናችንን የሳትንለትና የተሰደድንለት ድርጅታችን ያ! እኛ የምናውቀው ኢሕአፓ ሞቶብናልና!! ዕርማችንንም ካወጣን ዓመታት ተቆጥረዋልና። ለዚህ ቃላችን፤ እማኛችን ነው ምርኮኛ!**

ምርኮኛ የሚያወጋን ተወልዶ፤ ታግሎ፤ ተሰውቶ በትግሉ ትንቅንቅም ስለተሸነፈውና ስለወደቀው - የዛን ዘመኑ ኢሕአፓ ኢሕአፓውያን ታሪክ ነውና። አዎን ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነበር እንላለን፤ ከነክብሩ፤ ከነግራማ ሞገሱና ከነስህተቱም አምባገነኖችን ተናንቆ ያለፈውን የዚያን ዘመኑን ኢሕአፓ!! ለዚህ የምርኮኛ አንደምታ እና ለእኛም እምነት እማኝ እናቅርብ? መልካም፤ እነሆ ፈቃደን ከምርኮኛ፤

*"ፈቃደ…በመጋዘን ውስጥ ጉዞው የማያስበው የለውም፤ የትግሉን እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳልነበረ መሆንና የኢሕአፓን መበታተን ሲያስበው ግንባሩ ላይ ቁጥር ፈታ የሚለው የደም ስሩ ይግተረተራል፤ እልህ ይይዘዋል። የኢሕአፓ መዋቅር እንዲህ አንድ ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ቀርቶ በዓመታት ይበተናል ብሎ አላሰበም ነበር። ከጥይት ጋር ፊት ለፊት ይፋጠጥ የነበረ ሞራልና ወኔ እንዲህ በአጭር ጊዜ ይሟሽሻል ብሎ ገምቶ አያውቅም ነበር።…"*

ይህ ሐቅ እንጂ ፈጠራ አይደለም። ስለሐቀኝነቱም እንመሰክራለን። በቦታው ነበርንና፤ በመጋዘኑም ውስጥ አልፈናልና። እና በኒያ የሽንፈትና የሰቆቃ ወራት ከላዕላይ እስከ ታህታይ (ከማዕከላዊ ኮሚቴ እስከ ኢንተር ዞን፤ ዞን፤ ሪጅን፤ ሳብ ሪጅን፤ ዲስትሪክ እና ሴል ወይም ህዋስ ድረስ) የኢሕአፓ መዋቅር በአስገራሚና በአስደንጋጭ ፍጥነት ሲፈራርስም አይተናልና። እንደ ፈቃደ ሁሉ በዚያ አጭር ጊዜ የመዋቅሩን መበጣጠስና መመታት ማመን አቅቶን የቀን ቅዠት የሆነብን አእላፍ ነበርንና። ደግሞም ድሪቶ መኝታችን፤ ጋሬጣ አስቤዛችን ከርቸሌ መኖሪያችን ሆኖ ብዙ ዘክረንበታልና። ለእናንተ ግና፤ ዝርዝር ታሪኩን ምርኮኛ በዝርዝር አቅርቦታልና ከዚያው ማጣራት ይበጃል፤ ዕውነታውን ለመመርመር።

<u>ፍፁም ነው ዕምነቴ፤ የትግሉ ነው ህይወቴ</u>

ኢሕአፓ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ መዋቅሩን ለመዘርጋቱ ምናልባትም ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው የ1997 ዓ/ም የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

እስኳል የድርጅቱ አባላትም ይህንን ታሪካዊ አጋጣሚ በሚገባና በሚያስደንቅ ፍጥነት ተጠቅመውበታል፤ ድርጅቱን ለማስተዋወቂያና አባላትን ለመመልመያ። እና ፍሬህይወትም ዘማች ነበረች። እንንቀስ አብነት፤

*“ፍሬህይወት ከሥራ በኋላ ለሚደረጉት ስብሰባዎች ልዩ ፍቅር እያደረባት መጣ። ከ እነዚያ ስብሰባዎች ብዙ የማታውቃቸውን ነገሮች ተምራለች። ስለ መሬት ላራሹ፤ ስለ ተማሪዎች ንቅናቄ፤ ስለ ሕዝባዊ መንግሥት፤ ስለሩሲያና ቻይና አብዮቶች፤…በነዚያ ስብሰባዎች ምን የማይነሳ ነገር አለ። ፍሬህይወትን ግርም ይላታል።”*

ከዚህ አኳያ በዕድገት በህብረት ዘመቻ ወቅት የነበረውን የአስኳል ኢሕአፓውያንን አስደማሚ ድርጅታዊ ተግባራት ምርኮኛ በማራኪ ትረካው አንቆርቁሮታልና አንባቢያን የማወቅ ጥማታቸውን ከዚያው ከምንጬ በመቅዳት ይረኩ ዘንዳ ይቻላቸዋል።

እኒያ የዚያን ዘመኑ ኢሕአፓ ኢሕአፓውያን በርዕዮተ ዓለም ትጥቅ የካበቱ ብቻ ሳይሆን ተናግሮ የማሳመን ችሎታቸውም አስገራሚ ነበር። አብነት ይጠቅሷል፤

*“አንተነህ ስለጭቆና ሲናገር ተመስጦው በጣም ይደንቃል። ስለመደብ አፈጣጣር፤ ማህበረሰብ በመደብ ከተከፋፈለ በኋላ ስላለው የገዥና ተገዥ፤ የጨቋኝና ተጨቋኝ ግንኙነት ሲያስረዳ እርሱ ራሱ በዚያ ህይወት ውስጥ ያለፈ ነው የሚመስለው። ስለባላባታዊ ሥርዐት፤ የፖለቲካ፡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ሲተነትን ብዙዎች ገበሬዎች እስከማልቀስም ይደርሳሉ። ‘መሬት ላራሹ!’ በማለት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለስንት ዓመታት እንደታገሉ ሲገልፅ የደምስሮቹ ሁሉ በስሜት ይወጠራሉ።…”*

ኢሕአፓውያን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ገበሬውን በማደራጀትና መደባዊ ንቃተ ህሊናውን በማበልፀግ ረገድ የተጫወቱት ሚና ለደርግ አገዛዝ የራስ ምታት እስከሚፈጥርበት ድረስ ስለመሆኑ በታሪካዊ ዕውነታ የበለፀገው ምርኮኛ እንደ ምንጭ በጠራ ትረካው ዘግቦልናል።

ከዘመቻውም መልስ በየከተሞቹ በተቋቋሙት የወጣት ማህበራትም ሆኑ የሙያ ማህበራት ይካሄዱ በነበሩት ፖለቲካዊ ውይይቶች የኢሕአፓውያኑ ቅስቀሳ የብዙዎችን ቀልብ የገዛ እንደነበር ብቻም ሳይሆን አባላትን ለመመልመያም እንደ ‘ኢንኩቤተር’ ያገለገለ እንደነበርም ያወጋናል፤ ምርኮኛ።

ለመሆኑ ከእኒያ ኢሕአፓውያን ደም ጋር የተዋሃደው፤ ሁሉም በልቦናቸው የሚወርዱትና በአደባባይም ይዘምሩት የነበረው *“ለዘመናት በጭቆና ማቅ በግፍ ሠንሠለት ታስሬ፤ ጨቋኙን ልሽር፤ መብቴን ላስከብር ይኸው ተነስቻለሁ ዛሬ…/ ፍፁም ነው ዕምነቴ፤ የትግሉ ነው ህይወቴ…”* መዝሙራቸው ዕምነት ፅናት እንደምን ነበር የተገነባው? ብለን እንጠይቅ። እነሆ ለናሙና፤ ምላሹን ከምርኮኛ፤

*“ፍሬህይወት ሳታስበው በፖለቲካ መሳብ ጀመረች። አንተነህ የሚያመጣቸውን መፃህፍት በማንበብ ሌሊቱን ማገባደድ ለመደባት። ትናንሾቹን የማኦ ሴቱንግ መፃህፍት በጣም ወደደቻቸው።…ፖለቲካ መፃህፍት አንባቢነቷም በጣም ጨመረ፤ ፖለቲካም እያደር ስሜት እየሰጣት ሄደ።…”*

በዚያን ዘመን ኖሮ ያለፈው ኢሕአፓ አባላት በአባልነት ከመመልመላቸው አስቀድሞ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸውንና ርዕዮተ ዓለማዊ ብቃታቸውን ለማዳበር በጥናት ክበቦች ተይዘው የሚያሳልፏቸው እንቅልፍ አልባ ምሽቶች በርካቶች ነበሩ። በኢሕአፓዊነት ከተመለመሉም በኋላ አባላቱ ለድርጅታቸው የነበራቸው ፍቅር ወደር አልባ ነበር። እንንቀስ አብነት፤

"ለድርጅታቸው የሚገባውን ወርሃዊ መዋጮ ለመክፈል አስታዋሽ አያስፈልጋቸውም። ድርጅታቸውን ለማጠናከር የሚገባውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ የሚል የለም። ምንኛቸውም የግል ገቢ የላቸውም፣ ከቤተሰብም እንኳ በቋሚነት የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ አያገኙም፣ ግን እንደምንም ብለው...አሮጌ ልብሶቻቸውንና ጫማዎቻቸውን ሸጠው ...ለድርጅታቸው መስጠት ከምንም በላይ ያረካቸዋል። እርስ በርሳቸው ያላቸው መተሳሰብ ልዩ ነው። አንዳቸው ለሌላቸው ህይወታቸውን እንኳ ቢሆን እስኪሰጡ ድረስ ፍቅራቸው የጠነከረ ነው።..."

የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን ኢሕአፓን የገነቡት እንዲህ ነበር፣ አዎ! ይህም ዕውነት ነበር። ይብቃንና እንዲህ ያለው ሀቅ፣ እናምራ ወደ ሌላ ነቁጥ፣

በዚያን ዘመን የኖረውን የኢሕአፓን ልሳን 'ዴሞክራሲያ' ያነበበ ሁሉ በልሳኑ 'ምትሃታዊ ሃይል' ተቀፍድዶ ምርኮኛ ከመሆን አያመልጥም ነበር። በሺህዎች እንደሚቆጠሩት የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን ሁሉ ፍሬህይወትም የዴሞክራሲያ ምርኮኛ ከመሆን አላመለጠችም። የሚከተለውን ያነቧል፣

"በርካታ የዴሞክራሲያን ዕትሞች አነበበች። ከማይነጥፍ የፖለቲካ ዕውቀት ምንጭ ለሚጨለፋትና በየዕትሙ ለሚወጡት ፅሁፎች የምትሰጠው ግምት ከምንም በላይ ሆነባት። ዴሞክራሲያን የሚፅፉ ሰዎች ይደንቋታል፣ በየጊዜው የሰው ስሜት የሚሰርቁ የተለያዩ ፅሁፎችን የመፃፋቸው ነገር እጅጉን ይገርማታል። በዐይነህሊናዋ ልታያቸው ስትሞክር የሚታዩአት ማርክስ ኤንግልስና ሌኒን ናቸው። ልክ እንደነሱ ፂማምና ግዙፍ ይመስሏታል።

'ግን በናትህ...ይህንን የሚፅፉት ሰዎች የት ነው ያሉት?' አለችው አንድ ቀን ጋዜጣውን ሲሰጣት

'ሁሉም ቦታ' አላት ከልቡ እየሳቀ።

"እግዜር ናቸው ማለት ነዋ' አለች እርሷም እየሳቀች"

አዎ! እርግጥ ነበር። ዴሞክራሲያ አንዳች ምትሃት የነበረው የዚያን ዘመን የኢሕአፓ ሃይለ መንፈስ ልሳን ነበርና።

በኒያ የወታደራዊው መንግሥት አገዛዝ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ድርግም ብሎ ባልጠፋው የዴሞክራሲ መብቶች ቀዳዳዎች (እዚህ ላይ አምባገነኖች ሥልጣናቸው እስኪደላደል በዴሞክራሲ ሽርፍራፊ መብቶች እንዴት እንደሚቆምሩ ከኢህአዴግ የመጀመሪያዎቹ የአገዛዝ ዓመታት ጋር የደርግን ያነፃፅሯል) በዘመኑ የነበሩት የኢሕአፓ አመራሮች ለፓርቲው ሕዝባዊ ሃይል በማሰባሰብና ዓላማውን በሕዝብ ውስጥ በማስረፅ ረገድ በሚገባ ተጠቅመውባቸው ነበር። የጎህ መፅሄትን ለአብነት ያቀርቧል፣ ከምርኮኛም ይነቅሷል፣

"ለነሚሚ 'ጎህ' ማለት ተወዳጁ የጊዜው መፅሄት ነው። ጎህን አግኝቶ ሳያነብ የሚያስቀምጥ ማን አለ? ጥቂት ከቆየ እንደሚወሰድና ላይመለስም እንደሚችል ስለሚገመት እጅ ከገባ ማንበብ ነው። በጎህ መፅሄት ላይ ምን የማይወጣ ነገር አለ? ምን የማይተነተን የፖለቲካ ጉዳይ አለ? ትረካዎቹና ልቦለዶቹ ልብን ይነካሉ፣ ግጥሞቹ ስሜትን ይቀሰቅሳሉ፣ ትንታኔዎቹ ዕውቀት ያስጨብጣሉ።..."

ስለዚህ የምርኮኛ ትረካ ሀቀኝነት የእማኝነት ቃላችንን እንሰጣለን፤ እኛ። ልዩ መስህብ የነበራት ጎህ መፅሄት ታትማ ለገበያ ስትወጣ የነበረውን ትርምስና አግኝቶም የማንበብን ጉጉት ሃያልነት ዛሬ በህይወት ያለን የዛን ዘመኖቹ ሁሉ በአግራሞት የምናስታውሰው ነው። በበኩሌ ከስንትና ስንት ዓመታት በፊት በጎህ መፅሄት ላይ ያነበብኩት የ'ቱሉ ፎርሳ' ታሪክ ዛሬም ድረስ ከህሊናዬ ማህደር እንደተከተበ ይገኛል። በዚያን ዘመን ኖሮ ያለፈው ኢ.ሕ.አ.ፓ በእርግጥም ታላቅ የዕውቀት ጎተራ የነበረ ፓርቲም ነበር። ዛሬ ይህ ሁሉ ታሪክ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓ ታሪክ ነው። ማራክሳዊ ርዕዮትን መመሪያው አድርጎ የተነሳና የታገለ ፓርቲ! ዛሬ ኮሙኒዝም ወድቋል። የኢ.ሕ.አ.ፓም መሠረቱ ወድቋል። ኢ.ሕ.አ.ፓም እንደ ኢ.ሕ.አ.ፓነቱ አክትሟል። ከነብርታቱ ከነድክመቱ በአንድ የታሪክ ወቅት የነበረ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ተብሎ በታሪክ ይዘከራል! ይህ ታሪኩም በምርኮኛ ውስጥ ተናኝቶ ይገኛል፤ የመፅሀፉን አንባቢ እየጠበቀ።

እነሆ በምርኮኛ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው የዚያን ዘመን ኢ.ሕ.አ.ፓውያን *"...ፍፁም ነው ዕምነቴ፤ የትግሉ ነው ህይወቴ..."* እያሉ በመዘመር ወደር አልባ ስቃይንና መስዋዕትነትን በፀጋ የተቀበሉት በተሰለፉበት የፖለቲካ መስመርና በፓርቲያቸው ላይ በነበራቸው ፍፁም ዕምነት ይህም ዕምነት ከዕውቀት የተቀዳ፤ በዕውቀትም የዳበረ በመሆኑ እንደነበር ምርኮኛ ካቀረበልን ሠፊ የታሪክ ባህር የጨለፍነውን በዚሁ እንገታለን።

## ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ

የኮሎኔል መንግሥቱ ሃይለማርያምን አምባገነን መንግሥት ለመጣል የታገለው የዛን ዘመኑ ኢ.ሕ.አ.ፓ የትርፍ ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም። ኢ.ሕ.አ.ፓውያኑም የትርፍ ጊዜ አባላትና ታጋዮች፤ የፓርቲው መሪዎችም የትርፍ ጊዜ አታጋዮች ከቶም አልነበሩም። ሙሉ ጊዜያቸውን፤ ጉልበታቸውን፤ ዕውቀታቸውን፤ ገንዘባቸውንና ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። ይህ የማይካድ የማይነቃነቅ ዕውነት ነው።

በትንቅንቁ ኢ.ሕ.አ.ፓ በደርግ ተሸንፎ እስከተመታበት (1970 ዓ/ም መጨረሻ?) ድረስ የዚያን ዘመን የኢ.ሕ.አ.ፓ መሪዎች በቆራጥነት ታግለው እንደ አባላቱ ሁሉ መስዋዕትነትን ከፍለው አልፈዋል፤ ብዙሃኑ። ፓርቲያቸውንና ጓዶቻቸውን አደጋ ላይ ላለመጣል በደርግ የስለላ ሃይሎች እጅ ከመውደቅ ይልቅ ራሳቸውን የሰዉ ብዙዎች ሲሆኑ ከፎቅ ተወርውረው ራሳቸውን ከገደሉት መካከል ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይን ያስታውሷል። በቀጥታ ከዛን ዘመን የህይወት ገጠመኝ መጥቀስ ከተፈቀደልኝ ደግሞ ለአብነት ያህል በየካቲት 1970 ዓ/ም ፍልውሃ ላይ ሁለት ኢ.ሕ.አ.ፓውያንን ከከበቡት የደርግ የስለላ አባላት ለማምለጥ በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ጥይት ቢያልቅበት በእጅ ቦንብ ራሱን ያጠፋውን ይስሐቅን (ዕውነተኛ ስሙ ነው) ያቀርቧል። ይህንን የመሳሰሉትን የዚያን ዘመኑን ኢ.ሕ.አ.ፓ መሪዎችና አባላቱን የትግልና የመስዋዕትነት ሀቅ ነው ምርኮኛ የዘከረው። እነሆ ለንዑስ ርዕሳችን ከሰፊው የስቃይና የመስዋዕትነት ባህረ ታሪክ፤ ከምርኮኛ፤ ናሙናዎችን እንቀንጭብ።

*"ወ/ሮ ስርጉት ጩኸቱና ግርግሩ ወደተበራከተበት ሄዱ።...ሁለት ወጣቶች ወድቀው ተመለከቱ። ወንድማማቾች ናቸው። 'እናታችሁ ዝርግት ትበል' አሉ ደረታቸውን እየደቁ።...የበርካታ ቤቶች ደጃፎች አስከሬን ወድቆባቸዋል።...የአንድ ቤተሰብ ሶስት ልጆች ተገድለው ከቤታቸው አቅራቢያ ተጥለዋል...የካ ሚካዔል ለወጣቶቹ ቀብር በተሰበሰበ ህዝብ ተጥለቀለቀ...ያውም የወጣት ቀብር!...በአንድ አካባቢ ብቻ አስር አዳዲስ የቀብር ቁልሎች ተደረደሩ። ማንም ሳያስተባብረው ሀዘንና ምሬት የፈጠረው የተቃውሞ ሠልፍ ተጀመረ። ወጣቶች መፈክሩን ያንበለብሉታል፤ እናቶች እንባቸውን እያዘሩ ይቀበላሉ። እንደ እናቶች አይብዙ እንጂ አባቶችም በሠልፉ ውስጥ ነበሩ።"*

ዘመነ ፅልመት። ደም እንደ ጎርፍ የፈሰሰበት። የሰው ልጅ አስከሬን እንደ ድርቆሽ የተሰጣበት። ወላጅ ልጁ ለሞተበት የጥይት ዋጋ የከፈለበት።...ዘመነ ጭራቅ። ዘመነ ደርግ።

ግና ትግሉ አልቆመም። መስዋዕትነቱም አላባራም። ኢሕአፓውያኑ እየሞቱ ይታገላሉ። እየሞቱ ይሰለፋሉ። እየተሰለፉም ይዘምራሉ፤ *"...ቢሰበር አጥንቴ፣ ቢንቆረቆር ደሜ/ ፍፁም ነው ዕምነቴ፣ የትግሉ ነው ህይወቴ/ ልጓዝ በድል ጎዳና፣ በወደቁት ጓዶች ፋና..."* እያሉ። እናቶችም ይሰለፋሉ። የልጆቻቸውን መፈክር እያስተጋቡ፤ በእንባ እየታጠቡ። ዘመነ ዋይታ። ደርግም 'ዴሞን በዴሞትፈር' እያለ ለእድሜው መሰንበቻ በጅምላ ወጣቱን ማፈስ፣ ማሰርና መግደሉን ተያያዘው። እንጥቀስ ከምንጫችን፤

*"...አፈሳው ተጣጡፏል። በአንድ ቀን ብቻ መርካቶ አካባቢ በተደረገው ሠላማዊ ሠልፍ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታፍሰው ጃንሜዳ ታጎሩ።...በተከታታይ በየአካባቢው በተደረጉ አፈሳዎች የተነሳ የግንኙነት መስመሮች ተበጣጠሱ። ቀይ ሽብር አገሩን አናወጠው። የወላጅ እጣ ፈንታ ...የተጣለ የወጣት ሬሳ ማየት ሆነ። ነፍሰ ጡር እናቶችም ሳይቀሩ የቀይ ሽብር ሠለባ ሆነው ዋይታ ከተማውን ሞላው..."*

ምንም እንኳን ምድር ቀውጢ ብትሆንም፤ አፈሳው ሳያባራ ቢቀጥልም፤ በየአደባባዩ የጓዶቻቸው ሬሳዎች ቢዘረጉም፤ እስሩ ቢጧጧፍም፤ ለጊዜው ከአደጋው የተረፉት ኢሕአፓውያን - እነፍሬህይወት - የሚበጣጠሰውን ድርጅታዊ መዋቅር ሠንሠለቶች ለመቀጣጠልና የዕለት ተዕለት የፓርቲውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመፈፀም ከመባዘን ግን አፈግፍገው ቤታቸው አልተከተቱም፤ በፍፁም! ተራቸው ደርሶ ወይ በአፈሳ፣ ወይ በቀይ ሽብር አልያም በእስር እንቅስቃሴያቸው እስኪገደብ። ቃል ለትግሉ፤ ቃል ለፓርቲያቸው፤ ቃል ለጓዶቻቸው አለባቸውና...እነሆኝ ናሙና፤

*"ምንድን ነው የምናገረው? እከሌ እከሌ እያልኩ የሰው ስም ልዘረዝር በፍፅም አላደርገውም።...እስክሞት ድረስ እንኳን ቢሆን...*

*"/ፍሬህይወትን/ እግሯ ደንዝዞ የእርሷ እስከማይመስላት ድረስ እየተፈራረቁ ቀጠቀጧት። ዓይኖቿን ጨፈነቻቸው፣ በዓይነ ህሊናዋ እንደገና እናቷንና ሌሎቹን አየቻቸው...ጃኬቱን እስከ አንገቱ የቆለፈው ያ መኪና ውስጥ የነበረ ልጅ ታያት። እግሮቹና እጆቹ የታሰሩበት ብረት ቅጭልጭልታ በጆሮዋ ተሰማት። ከማበጣቸው ብዛት እንደመስታወት የሚያብለጨልጩት የዳኙ እግሮች።...ቀዝቃዛ ውሃ በእግሮቿ ላይ ተደፋ። ዓይኖቿን ገለጠች። ከእግሮቿ የሚወርደው ውሃ በዐይኖቿና በአፍንጫዋ ውስጥ ገባና አፈናት።...አለንጋው እንደገና እየተከታተለ እግሮቿ ላይ አረፈ። አቤት ስቃይ!...ሰውነቷ ሲደነዝዝ ደስ አላት። ቀስ በቀስ እንቅልፍ ውስጥ የገባች መሰላት። ሁሉም ነገር ጭልምልም አለ።..."*

## <u>ቅድመ መቋጫ</u>

አንባቢ ሆይ! ፍሬህይወት በደርግ እጅ ከወደቀች በኂላ ከተቀበለችው መጠነ ሰፊ ስቃይ ለናሙና የነቀስነው ሲሆን አሰቃቂነቱ ከዚህ በከፋ ደረጃ የተተረከባቸው በርካታ የሌሎች የምርኮኛ ታሪከኞች ታሪክ በመፅሀፉ ውስጥ በስፋት ይገኛል። በስድስት ሰፋፊ ክፍሎች በ491 ገፆች የወረደው ታሪክ ወርድና ጥልቀት አለውና አንባቢያን ከምንጩ ገብተው መኮምኮም ይቻላቸዋል።

ይሁንና እንዲህ የመሰለውን የዚያን ዘመን ኢሕአፓውያን ሠቆቃ መቀበል ወይንም እንዲህ የመሰለ ቶርቸርን የመቻልና የዓላማ ፅናት መኖር በርግጥ በዛን ዘመን

ኢ.ሕ.አ.ፓ.ውያን ላይ ነበርን? ብለው ራሳቸውን የሚጠይቁ የዚህ ቅኝት ታዳምያን (ምርኮኛን ያነበቡም ሆነ ያላነበቡ) ሊኖሩ እንደሚችሉ እገምታለሁ። ለዚህም ዋናው ምክንያት ደራሲ ቆንጅት የምርኮኛን ታሪክ በማያሻማ ቋንቃ በግልፅ ልቦለድ አለመሆኑን ባለማስቀመጣቸው ሲሆን (ምንም እንኳን በመፅሀፉ መጀመሪ ላይ ደራሲ ቆንጅት ለስራቸው በተባባሯቸው ሰዎች ምሥጋና ላይ እንዲሁም 'ፍሬህይወት ማን ናት?' በሚለው ቅድመ ትረካ ላይ ካቀረቡት ገለፃ ይዘት ዕውነተኛ ታሪክነቱን መረዳት ብንችልም ቅሉ) ምናልባት በተከታታይ የምርኮኛ እትሞች ይህንን እንደሚያስተካክሉ ተስፋ እያደረግሁ ምርኮኛ ከዕውነት የተቀዳ ዕውነተኛ ታሪክ ስለመሆኑ ግን እጅግ በጣም ጥቂት ማስረጃዎችን ከህይወት ልምድ በማከል የምሥክርነት ቃሌን እሰጥ ዘንዳ የአንባቢያን ፈቃድ ይሁንልኝ።

እነሆ ምሥክርነት፤

የደርግ ማዕከላዊ ምርመራ ቅርንጫፍ በነበረው በከፍተኛ 25 (በዛን ዘመኑ አጠራር ነው፤ የአሁኑን አላውቀውምና) እጅግ ሰፊ የመጋዘን እስርቤት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኢ.ሕ.አ.ፓ.ውያን (ሴቶች የታሰሩበትን ክፍል አሃዝ ሳይጨመር) በደርግ ሰላዮችና መርማሪዎች እጅ ወድቀው ወደር አልባ ስቃይና እንዲሁም ሞት የተቀበሉበት ጉሮኖ ሆኖ ከ1970ዓ/ም መጀመሪያዎች እስከ 1971 ዓ/ም መጀመሪያ ገደማ ቆይቷል፤ በአጋጣሚ ቀይ ሽብር በድንገት በመቆሙ በህይወት የተረፉት ወደ ከርቸሌ እስከወረዱበት ድረስ።

በከፍተኛ 25 የሠቆቃ መጋዘን ውስጥ በመላው ሀገሪቱ ከነበሩት በርካታ እስርቤቶች ይበልጥ በኢ.ሕ.አ.ፓ.ና በሊጉ ውስጥ ከፍተኛ ሃላፊነት የነበራቸው ኢ.ሕ.አ.ፓ.ውያን የሚገኙበት ነበር። በፓለቲካው መዋቅር ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት እስከ ኢንተር ዞን፤ ዞን፤ ሪጅን፤ ሳብ ሪጅን እና ዲስትሪክት ፀሀፊዎችና የኮሚቴ አባላት፤ በከተማው የትጥቅ ትግልም ከፍተኛ ሚሽን ላይ የተሳተፉ (ለምሳሌ በኮሎኔል መንግሥቱ የግድያ ሙከራ) የስኳድ አባላትና ኮማንደሮች፤ እንዲሁም በትጥቅ ፕሮፓጋንዳ (አርምድ ፕሮፓጋንዳ) ኮሚቴዎች ውስጥ ያገለገሉ የኢ.ሕ.አ.ፓ. አባላት ቁጥር እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም፤ በከፍተኛ 25 የ ሠቆቃ መጋዘን ውስጥ። በዚያ ታላቅ መጋዘን ውስጥ መኻል ለመኻል ጉብ ያለ ጉርድ በርሜል ይገኛል። ያ ሁሉ እስረኛ ፊኛውን የሚያስተነፍሰው በዚሁ በአንድ ጉርድ በርሜል ላይ በመሆኑ በርሜሉ ይሞላና ሲሚንቶውን ያጥለቀልቀዋል። የሽታውን ነገር ቃላት አይገልፁትም። በአጭሩ መጋዘኑ ሽንት ቤትም ነበር ቢባል አንባቢ ማጋነን እዳይመስለው! ዝርዝሩን ለታሪክ ትቼ ልቀጥል።

እንደ ፍሬህይወትና በርካቶች የምርኮኛ ታሪከኞች ሁሉ የግፍ ስቃያቸው ወደር ካልነበረው የከፍተኛ 25 ታሳሪ ኢ.ሕ.አ.ፓ.ውያን መካከል፤

የፓርቲውን ምሥጢርም ሆነ አብረዋቸው የሰሩትን ጓዶች ስም ላለማውጣት በግርፍ /ቶርቸር/ ላይ ከሞቱት ለአብነት የፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እንደነበር በመረጃ የታወቀው ብርሃኑ (የኮድ ስሙ ሊሆን ይችላል) አንዱ ሲሆን፤

በግርፋት /ቶርቸር/ ብዛት አካለ ጎደሎ ከሆኑት የፓርቲው ከፍተኛ አካለት ደግሞ ነስሩ ዑመር እና ታደሰ ጢዮን፤ ወይንም የፓርቲውን ምሥጢር እንደጠበቀ ህይወቱን ለማጥፋት ከፎቅ ተወርውሮ የአካል ጉዳት ቢደርስበትም እንደዛም ሆኖ ከሆስፒታል አውጥተው በከፍትኛ 25 አረመኔዎች ቶርቸር የተሰቃየውና የእድሜልክ አካለ ጎዶሎ የሆነውን እርቃለሁ ወይሞን፤ ወይንም ከውስጥ እግሩ እስከ ጀርባ አካሉ በደረሰበት አሰቃቂ ግርፍ ሰውነቱ ደም እያዠና ነፍሳት እየፈጠረ የተሰቃየው በተለያዩ የፓርቲው ወታደራዊ ተልእኮዎች (ለምሳሌ ከእነ ጎይቶም ባራኪ /ለባሲ?/ ጋር በመንግስቱ ሃይለማርያም የግድያ ሙከራ መሳተፍ፤) ታላላቅ ግዳጆችን የተወጣው ኮማንደር ሱራፌል ካባን፤ ወይንም

በግርፋት ብዛት እግሮቻቸው እንቆሰሉ በውድቅት ሌሊት በእነሳሙና (የዋናው መርማሪ ቅፅል ስም ነው) ከመጋዘኑ እየተጠሩ ከተረሸኑት ለምሳሌ የፓርቲው ኢንተርዞን ሙሁዲን ዑመር፤ የሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሙሉዓለም /ምንውዬልህ?/ እና እጅግ በርካቶች (ስማቸውንና የስቃዩን አይነት መዘርዘር የማልችለው) ለምርኮኛ ታሪክ ሀቀኝነት የማቀርባቸው የዛን ዘመን ኢሕአፓውያን ታሪክ ነው። ከሌሊት ርሸናዎች የተረፉት በመቶዎች የሚቆጡት የከፍተኛ 25 እስረኛ ኢሕአፓውያን ከርቸሌ ወርደው ለዓመታት ማቅቀዋል፤ እንደ ምርኮኛ ታሪክ ታሪከኛ ኢሕአፓውያን። እና ዛሬ ያ! የህይወት መስዋዕትነት ደግሞም የአካልና የህሊና ስቃይ የከፈልንለት፤ ያ! ታግሎ ያታገለን ኢሕአፓ ታሪካዊ ግዳጁን በዚያ ዘመን ጨርሶ ሞቷል ብለን ስንመሰክር ሞቱን ሞተን እስሩን ታስረን በአይናችን ያየነውን በህይወትም ያለፍንበትን ዕውነታ አንተርሰን እንጂ በስሜት ተነድተን አልያም ከህሊናችን ውጪ በሌላ ሃይል ቹ ተብለን አይደለም፤ በፍፁም!! ከሁሉም በላይ ግን ይህንን የምሥክርነት ቃል በአደባባይ የሰጠነው ያ! የምናውቀውን ኢሕአፓ እና የኒያን ሰማዕታት ኢህአፓውያንን ክብር የመጠበቅ የታሪክ ግዴታም ስላለብን ነው!!

<u>**መቋጫ**</u>

አንባቢ ሆይ! እነሆ በ491 ገፆች የተካተተውን የምርኮኛን መፅሀፍ ወፍ በረር ቅኝት ፈጠምን። ለመሆኑ የዚህ ቅኝት ፋይዳ ምን ይሆን? ሁለት ዒላማዎች አሉት።

ቀዳሚ፤ ምርኮኛን ላላነበቡ የዚህ ቅኝት ታዳሚያን ምርኮኛን ማንበብ አስፈላጊነቱን ለማሳየትና መፅሀፉን አድኖ የማንበብ ስሜትን ለማቀጣጠል፤

ተከታይ፤ ኢትዮጵያችን ከደርግ አምባገነን አገዛዝ ወደ ህወሃት/ኢህአዴግ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ነው የተሸጋገረችው። አምባገነኖችን አስወግዶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም አስተዳደር የመመስረቱ የእነፍሬህይወት ዓለማና ትግል በዚህ ዘመን ያለው ትውልድም ዓላማና ትግል ነው። በዚህ ዘመን የሚጠይቀውን ትግል በድል አድራጊነት ለመወጣት የሚከፈለውም መስዋዕትነት ውጤት አልባ ሆኖ እንዳይቀር እነፍሬህይወት ከከፈሉት ፍሬ አልባ መስዋዕትነት ምን ትምህርት መቅሰም ይቻላል? ኢሕአፓ ታላቅ ፓርቲ ነበር፤ ድፍን ጦቢያን ያስተባበረ፤ የህዝብ ፍቅርም የነበረው። ለምን ወደቀ? የህዝብ ፍቅሩና የሃይል ምንጩስ እንዲያ የገነነው ለምን ነበር? ዳግም በዚያ መልክና በዚያ ሃይልስ መነሳት ለምን አልቻለም? ከኢሕአፓ የአደረጃጀት፤ የሀይል አጠቃቀም የትግል ስልትና የመስዋዕትነት ታሪክ ተምረን ወይም መርምረን ለዛሬው ትግል ምን አይነት አደረጃጀትና የትግል ቅያስ ያስፈልገናል? ከሁሉም በላይ የዚያን ዘመኑን የኢሕአፓውያንን ዓይነት የትግል ፅናትን የዓላማ ዕምነት በአሁኑ እልህ አስጨራሽ ትግል በሚሰለፉት ሃይሎች ውስጥ እንዲኖር ምን መደረግ ይኖርበታል? ዛሬም እንደነፍሬህይወት ዘመን '...ፍጹም ነው ዕምነቴ፤ የትግሉ ነው ህይወቴ...' ብለው እስከመጨረሻው በትግሉ ጎራ የሚቆሙ ሃይሎችን ለማሰማራት የሚቻለው እንዴት ብንደራጅ ብናደራጅና ብናስተምር ነው?...ምርኮኛን አንብበን በህሊናችን መመላለስ ከሚጀምሩት ጥያቄዎች ጥቂቶቹ ናቸው። የዚህ ቅኝት ሁለተኛ ዒላማም እኒህና መሰል ጥያቄዎችን በየጎራችን አንስተን አደብ በገዛና በሰከነ መልኩ እንድንመረምርና እንድንማማር እንዲያም ሲል ወደ ተግባር እንድናመራ ጥርጊያ ለመስጠት ነው።

የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝን ለመጣል በሚያስተባብረው ድርጅት ዓላማ ዙሪያ የሚሰለፉ ታጋዮች እንደነፍሬህይወት ሁሉ እንዲህ እያሉ መዘመር ይጀምሩ ይሆን?

ለዘመናት በአምባገነን ሠንሠለት ታስሬ
በወያኔ ግፍ ማቅቄ፤ ነፃነቴን ተገፍፌ፤

ይኸው በቃኝ! ብያለሁ ዛሬ
ተነስቻለሁ አምርሬ፤

ለኢትዮጵያ ትንሳዔ፤ ፍፁም ነው ዕምነቴ
የትግሉ ነው ህይወቴ፤ አርነት ነው ግባቴ፤
ቢንቆረቆር ደሜ፤ ቢወቀጥ አጥንቴ
በአምባገነን በወያኔ
ፍፁም ነው ዕምነቴ፤ ለኢትዮጵያ ትንሳዔ
የትግሉ ነው ህይወቴ፤ ነፃነት ነው ግባቴ።

ወያኔ ይፍራ ይሸበር
የአድርባይ ቅስሙ ይሰበር።
ይኸው በቃኝ! ብያለሁ ዛሬ
ተነስቻለሁ አምርሬ።
የትግሉ ነው ህይወቴ፤ ነፃነት ነው ግባቴ
ለኢትዮጵያ ትንሳዔ፤ ፍፁም ነው እምነቴ!!

በመጨረሻም፤

የትውልድን አደራ ለትውልድ ለማስተላለፍ ምርኮኛን ያቀረቡልን ደራሲ ቆንጅት ብርሃን እና በመረጃዎች የተባበሯቸው የዚያን ዘመን ኢሕአፓ ኢሕአፓውያን ሁሉ ለዚያ ዘመን ትውልድ ባለውለታ ናቸውና፤ እኔም በዚያ ዘመን ትውልድ አካልነቴ ልባዊ ምሥጋናዬ በያሉበት ይድረስልኝ እላለሁ።

በያለንበት ቸር ይግጠመን!
መስፍን ማሞ ተሰማ
ጥር 2004 ዓ/ም
ጃንዋሪ 2012

ሲድኒ
አውስትራሊያ

የምርኮኛ አድራሻ፤ ስልክ (ሞባይል) 0911405427

Email: Merkognakon@Gmail.Com

በቅኝቱ ላይ ለሚኖርዎ አስተያየት፤ አድራሻዬ ይኸውልዎ፤ mmtessema@gmail.com